## ተው አታበሳጩኝ ነፍስ እንዳትዘሩብኝ

ሃያ ስድስት (26) ዓመታት፣

አስረውኝ በግዞት፣

ህሌናየን ሰልበው፣

ለዓለምም አስታውቀው፣

እንደሆንሁ የቁም ሙት፣

እነሱ ሳያውቁ በአምቦ የነደደው፣

ጭሱን በወልቃይት፣ ጎንደር ውሥጥ አየሁት።

## ተው አታበሳጩኝ ነፍስ እንዳትዘሩብኝ

ለወገኔም ሁሉ አስመስለው እውነት፣

ጽፈው በጋዜጣ አስሙቱ ነጋሪት።

መልዕክቱ እንዲታወቅ ቀንም ሆነ ሌሊት፤

ሁሉ እንዲገነዘብ ውንድም ሆነ እሴት።

መሰንቆ ከጠፋ በታምቡር አስረዱት፤

ከዛሪ ጀምሮ ደንግገናል አሉት፣

ማንም አያታልህ ያንተ አገር ክልል ናት።

ሃያ ስድስት (26) ዓመታት፣

እያሉ “አንድ ላምስት”፣

ሂሳብ ቆጣሪውን ሁለት፣ ሶስት፣ አራት

ብሎ ማስረዳትን አንዳያውቅ አረጉት።

## ተው አታበሳጩኝ ነፍስ እንዳትዘሩብኝ

ማን አለብን ብለው ወሪውንም ነዙት

እንድናመሰግን የነሱን ሥጦታ

እኔ አውቃለሁና እያሉ ነገሩን

ምን እንደሚበጅህ ፣

ከዛሪ ጀምሮ አዲስ ስም ሰጠሁህ፤

ደግሞም አዲስ ፈሊፕ እኔ ቀየስሁልህ።

ሕሌናቸው ዞሮ ባማጉት መድኃኒት

ሐሰትን ሸፍነው አስመስለው እውነት፤

ማን አለብን ብለው ገበሪውን ሳይቀር

ዘር አትዘራም አሉት።

ድሮም ማረስ አታውቅ

በዱር በገደሉ ከብትን እየነዳህ፣

እርቅናም በዝቶብህ፣

አንተ አይደለህም ወይ

በርሃብ የተማቀቅህ፤

ይልቅስ መርቀኝ እኔ ላደረግሁልህ።

ክልል ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚም እድገት፤

መሪትህን ወስጀ "እንድትሰለጥን"

ለፈረንጅ ሰጠሁት።

**ተው አታበሳጨኝ ነፍስ እንዳትዘሩብኝ**

ብገደልም እንኳን ትንሳዬ እውን ነው፤
እነሱ ሳያውቁ በአምቦ የነደደው፣
ጭሱን በወልቃይት፣ ጎንደር ውሥጥ አየነው።
በደቡብ፣ በሰሜን፣ በምሥራቅ፣ በምዕራብ ኢትዮጵያ፤
እንዲህ ሲል ሰማሁት ወጣቱ ቡቃያ።
የጨለማ ጉዞ ምንም ብትለምዱ፣
ቀኑ ሳለላችሁ ተው ተመከሩ፣
ሐገር የጋራ ነው፣ አይደለም የግል ሐብት፤
ባዋጅ አስመትቶ፣ ካድሬ የሚያዝበት።
አዛውንቶቻችን ያሉትን አስታውሱ፣
“አትምከር ይምከሩ፤
በቆፈሩት ጉድጓድ [ሳይቀበሩ] አይቀሩ”
ቀኑ ሳለላችሁ ተው ተመከሩ።

© ለምለም ፀጋው፣ January 11, 2018

Inspired by the article titled, “Ethiopia’s TPLF must fix its disease, not symptoms” (http://www.satenaw.com)